በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

እንኳን ለዓቢይ ጾም ሶስተኛ ሳምንት በሰላም አደረሳችሁ!!! የዚህ ሳምንት ስያሜ 'ምኩራብ' ይባላል፡፡ ምኩራብ (በጽርዕ “synagogue”) ከቤተ-መቅደስ በተለየ መልኩ የቦታ ወሰን የሌለው አጥቢያ የጸሎት ቤት ነው። በብሉይ ኪዳን ቤተ-መቅደስ ከኢየሩሳሌም ውጭ የማይሰራ ሲሆን ምኩራብ ግን አማኞች ባሉበት በየትኛውም ስፍራ ይሰራ ነበር፡፡ የሚሰራበትም ዓላማ ለሕገ አሪት መማሪያ እና ለቃለ እግዚአብሔር መነገሪያ ነበር፡፡ ቤተ-መቅደስ ለመስዋዕት ማቅረቢያነት ሲያገለግል ምኩራብ ግን ለቤተ-ጸሎትነት ብቻ ያገለግል ነበር፡፡ በዚህ ሳምንት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያንም ጌታ ድውያነ ነፍስን በትምህርቱ ለመፈወስ በምኩራብ ስለ ማስተማሩ ታወሳለች፡፡

ለሳምንቱ ይህን ስያሜ የሰጠው ቅዱስ ያሬድ በዚህ ሳምንት መድኃኒታችን በምኩራብ አይሁድ ተገኝቶ ስለማስተማሩ እና ለታሰሩት ነፃነትን፤ ለሞቱት ሕይወትን፤ ለድሆች ወንጌልን እንዲሁም በፍርድ ላሉት ሁሉ ዓመተ ምሕረትን መስበኩን ለዚህ ሳምንት ባዘጋጀው መዝሙሩ ላይ «ቦአ ኢየሱስ ምኩራበ አይሁድ.....»

> "ኢየሱስ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገባ የሃይማኖትን ቃል አስተማሩ ከመስዋዕት ምዕዋትን እወዳለሁ አላቸው፡፡ የሰንበት ጌታዋ የምሕረት አባትዋ እኔ ነኝ አላቸው፡፡ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉ ቤቴ የፀሎት ቤት ይባላል፡፡ ምኩራብ ገብቶ ተቆጣቸው ዝም ይሉ ዘንድ ትምህርቱን የቃሉን ሞገስ፣ የነገሩን መወደድ የአፉን ለዛ አደነቁ፡፡"

በማለት ጌታችን በምኩራብ ስለማስተማሩ ያብራራል፤ ወንጌላዊው ማቴዎስም "ኢየሱስም በምኩራቡ ቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝቡም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር" ብሎ ከቅዱስ ያሬድ አስቀድሞ ተናገረ፡፡ አይሁድ ፊት ለፊት ለታይታ ለከንቱ ውዳሴ በሚቀመጡባት ምኩራብ ክርስቶስ የነፃነትን ወንጌል እንደሰበከ ወንጌላዊው ሉቃስም "ኢየሱስም ወዳደገበት ወደ ናዝሬት መጣ፡፡ እንደልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ ሊያነብም ተነሳ፡፡ የነብዩን የኢሳይያስንም መጽሐፍ ሰጡት፡፡ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ ‹‹የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆችም ወንጌልን እሰብክ ዘንድ፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለእውሮች ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታ ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል›› ተብሎ የተፃፈውን ስፍራ አገኘ፡፡ መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ፡፡ በምኩራብ ም የነበሩት ሁሉ ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር፡፡ እርሱም ‹ዛሬ ይህ በጆሮአችሁ ተፈጸመ› ይላቸው ጀመር፡፡ ከአፉ ከሚወጣው ከፀጋው ቃል የተነሳ እየተደነቁ "ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን ? ይሉ ነበር" በማለት ጌታ በምኩራብ ውስጥ በስልጣን ያስተምር እንደነበር ይነግረናል፡፡ /ሉቃስ4÷14-23/

በቅዳሴ ጊዜ የሚነበበው ወንጌል የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2÷ 12-ፍጻሜ ሲሆን ጌታን በቤተ መቅደስ የሚፈጸመው የንግድ ስራ እንዳሳዘነው ገልጦ በጅራፍ መንጋዎቹን ከነጋዴዎቻቸው ጋር ከቤተመቅደስ እንዳስወጣና "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሶስተኛውም ቀን እኔ እሰራዋለሁ (አስነሳዋለሁ)" ብሎ ስለሞቱና ትንሣኤው እንደተናገረ ይተርካል፡፡ ይህን ለቤተ-መቅደሱ ያደረበትን ቅናት ደግሞ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት በዕለቱ ምስባክ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡- መዝ 68÷ 9

እስመ ቅንዓት ቤተከ በልዓኒ ፤ **የቤትህ ቅናት በልቶኛልና፤**

ትዕይርቶሙ ለአለ ይትዔየሩከ ወድቀ ላዕሌየ ፤ **የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወደቋልና፤**

ወቀጻእከዋ በጾም ለነፍስየ :: **ሰውነቴን በጾም አደከምኋት ::**

እንግዲህ ወንጌሉም ምስባኩም ጌታ ለቤተ-መቅደስ ያደረበትን ቅናት ይነግሩናል፡፡ ቤተ-መቅደስ የተባለው የሰው ልጅ ልቦና ሲሆን ፤ አይሁድ የዲያብሎስ፤ የአይሁድ ሸቀጥ ደግሞ የኃጢአት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በዚህም ጌታ ለኛ ያለውን ቀናኢነት እና ኃጢአታችንን ከልባችን ጠራርጎ ዲያብሎስን አዋርዶ እንዳባረረልን እናውቃለን፡፡

ወዳጆች ሆይ! አምላካችን የሚቀናለት የሕይወታችን ቤተ-መቅደስ የኃጢአት ገበያ እንዳይሆን ልንጠነቀቅ እና በዚህ ዓለምም ርኩሰት እንዳይበላሽ በንጽህና ልንጠብቀው ይገባል ፤ እግዚአብሔር አምላካችንም በቸርነቱ ይጠብቀን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!

ቅ/ጳ/ሕ/ግ/ጉባኤ ትምህርት ክፍል መጋቢት ፳፭ ፣ ፳፻፲፯ ዓ.ም